817
4916

ስምንተኛ ዓመት ቍ ፶፭

እ.እ.ሐምሌ ፩ ፺፯ ዓ.ም

# ዜና ቤተ ክርስቲያን ።

በወር አንድ ጊዜ ይታተማል የፖስታ ሳጥን ቍጥር 1283

በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ት/ ቤቶች ጽ/ ቤት ፣ በታሪክና ድርሰት ክፍል ኀላፊነት ።

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianortodox.org

ግንቦት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፫ ፡ ዓ.ም ፡
፳፩ ገ ፡ ሐሙ ፡ ፲፱፻፸፯

...ረታና ቤተሰብ
...ቤተ መጻሕፍት

## ስለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዓለ ልደት ።

ይህ በዓል ኢትዮጵያን ባዲሱ የሥልጣኔ ብርሃን ለማገናጸፍና ከድንቁርና ቅዝቃዜ ለይቶ በጥበብ ሙቀት ለማፋፋት እውነተኛው ፀሐይ የወጣበት ቀን መሆኑን ዓለም ሁሉ የሚያውቀው ስለሆነ ብዙ ሐተታ አያስፈልገውም ።

ሆኖም ይህ በምሥራቅ (ሐረር) የወጣው ታላቅ ፀሐይ ፤ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ብርሃኑ እየሰፋ ፤ ሙቀቱ እየገፋ በመሔዱ ብርሃንነቱ መላ ዓለምን አደረሰ እንጂ በኢትዮጵያ ብቻ ስላልተወሰነ ይህ ፀሐይ የመላው ዓለም ደስታ ነው ብንል አናፍርበትም ።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ብትሞት ያስነሣት ፤ ብትራብ ያመሰት ፤ እንዳትወድቅ የሚደግፋት ፤ እንዳትከሳ የሚያፋፋት ጌታዋን ያገኘችበት ቀን ስለ ሆነ ይህን በዓል ከሌላው አታወዳድረውም ።

ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያንም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ ከተመረጡበት ቀን ጀምሮ የዋሉላትን ውለታና ወዲያውም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ጐን ለጐን ሁና ለመታየት የሚያበቃትን ከፍተኛ ደረጃ ማስጨበጣቸውን እያሰበች ፤ ይህን ሁሉ ያደረጉላት በዚህች ቀን ተገኝተው ስለሆነ ይህችን ቀን ዕለተ ፍሥሐ ወሐሤት ዕለተ ክብር ወልዕልና እያለች ማሞገሷንና የዚችን ቀን ታላቅነት መስበኳን አታስታጉልም ።

ለዘላለሙም ጸግዎ ሰላመ ለንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ለታዕካሁ ወለሠራዊቱ ለመሳፍንቱ ወለመኳንንቱ እያለች ከ፹፪ተኛው ዓመተ ልደት ያደረሳቸው እግዚአብሔር ከንጉሣውያን ቤተ ሰዎቻቸው ጋር ጠብቆ መንበረ መንግሥታቸውን ሳያናውጽ ለዘላለም እንዲያኖርላት ጸሎቷን አታቋርጥም ።

ዛሬም ከሔዱበት መንገድ በሰላም መልሶ በዙፋናቸው እንዲያስገኝላት ምሕላዋን በመቀጠል ላይ ትገኛለች ።

## የቅዱስ ጳውሎስ በዓል አከባበር በሰዋስወ ብርሃን ።

፲፱፻፸፯ ዓ፣ ም፣ ሐምሌ ፫ ቀን ሰዋስወ ብርሃን ተብሎ በተሰየመው በቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ በዓል የሚደረግበት ቀን ስለ ነበረ ፤ በአቶ በትረ ጽድቅ ካሣ መሪነት የሰዋስወ ብርሃን ተማሪዎች ከበዓሉ ቀን አስቀድመው የቤተ ክርስቲያኑንና የትምህርት ቤቱን ዙሪያ በግጽዳት ሰንብተዋል ።

እንዲሁም ስለሐዋርያው ታሪክና ፤ ስለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወደ አሜሪክ መሔድና ስለግርማዊት እቴጌ መልክም ልግሥና የተዘጋጀውን መዝሙር በማጥናት ይገኙ ነበር ።

የበዓሉ አከባበርም በግርማዊት እቴጌ ሕሊና እጅግ የታሰበበት ስለ ሆነ ፤ ግርማዊት ፤ ሐምሌ ሦስትና ሐምሌ አራት ቀን ከቀኑ ከሥር ሰዓት በላይ በሰዋስወ ብርሃኔ እየተገኙ ተማሪዎቹ በመሪያቸው በአቶ በትረ ጽድቅ ካሣ አነቃቂነት ያከናወኑትን የጽዳት ተግባር ተመልክተው በሥራው አከናወን መደሰታቸውን ገልጠዋል ።

www.ethiopianortodox.org

## በዕለተ ዋዜማው ።

በዋዜማው ቀን የብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በመጡ ጊዜ የዋዜማው ጸሎት ተጀመረ ።

በዚህም ጊዜ ሊቀ መዘምራን አክሊሉ ገብረ ኪሮስ የሚቀጥለውን ቅኔ ተቀኙ ።

### ፈቀዱ ሐዋርያት ፤

ትትልዎሙ ድኅረ ወለተ ጊዮርጊስ እኅቶሙ ።
ለይእቲ እስመ ተደለወ ሃይማኖት ቤቶሙ ።
ወለምንት ብዙኅ ወለተ ጊዮርጊስ ትፃሙ ።
እምጣነ ሕጻጥ የአክል በከመ ሕጎሙ ።
ለዘአምነ ለክርስቶስ በስሙ ።

ከዚህ በኋላ ሰላሙ በዝማሜ ተብሎ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ አሳርገው ሠርሆት ተደረገ ።

## በዕለተ በዓሉ ።

በዓሉ በተከበረበት ቀን (ሐምሌ ፳) ከሌሊቱ በስድስት ሰዓት የደወል ድምጽ በተሰማ ጊዜ ፤ ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ፤ መምህራኑና ተማሪዎቹ የሰዓታቱን ጸሎት ጀምረው በትጋት እያገለገሉ አደሩ ።

የሰዓታቱም ጸሎት በተፈጸመ ጊዜ ምስባክ ተሰበከና ወንጌል ተነበበ ። ወንጌል ከተነበበ በኋላም ፤ ምልጣን ተመልጥኖ እስመ ለዓለም ተባለና ብዙ ድርሰት ደረሰ ።

በነግህም ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ፤ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ፤ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል መጥተው ልባዊ ጸሎት እያደረሱ ከቆዩ በኋላ ፤ በአንድ ሰዓት ከሩብ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀመረ ፤ በዚሁም ጊዜ ግርማዊት እቴጌ ፤ ልዑል አልጋ ወራሽ በብዙ ሠራዊት ታጅበው መጡና በማስቀደሻው ሥፍራ ቆሙ ።

ጸሎተ ቅዳሴው በተፈጸመ ጊዜም ፤ ከተማሪዎቹ አንዱ ክፍሌ እሸቴ የተባለው ወጣት ስለበዓሉ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ወደ ግርማዊት እቴጌ ፊት ቀርቦ አነበበ ።

ቀጥሎም ፡ ዕውራንን በዘመናዊ አቀድ ንባብና ጽሕፈትን ለማስተማር የተቋጠሩ ማቴዎስ ደምሴ የተባሉ መምህር ማየት የማይችሉ ሲሆኑ ፤ በዓይነ ሥውርነት ያዘጋጁትን ጽሑፍ በጥበባዊ ዘዴ ለማንበብ በመቻላቸው ሁሉን አስደነቁ ።

ከዚህ በኋላ ታቦቱ ወጥቶ ሥርዓተ ዑደት ተደረገና ጸሎተ ምህላ ደረሰ ። ከጸሎተ ምህላውም አደራረስ ቀጥሎ አምስት ወጣቶች ከዚህ የሚከተለውን ግሥ በሚያስደንቅ ዜማ አለዘቡ ።

### ግሥ ።

ዘመራሕከሙ ለሕዝብከ በየማነ እዴከ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ወለሐዋርያቲከ በባሕር ከነ ዛሕነ በቅድሜከ ።



ይእዜኒ ርድአነ በጸሎተ ባስልዮስ ስብሓት ለከ ፤ ወለንግሥትነ ወለተ ጊዮርጊስ ። ይህም በተባለበት ጊዜ ስለበዓሉ የታተመው መጽሐፍ ለሁሉም ታደለ ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ቅንዑ ለእንተ ተፀዉ ጸጋ ብለው የሐዋርያውን ቃል አርእስት በማድረግ ግርማዊት በየጊዜው ለሰዋስወ ብርሃን ያደረጉትን ልግሥና ፤ እንዲሁም ዘንድሮ የሰጡትን ተጨማሪ ሀብት በሐዋርያዊ ቃላቸው ገለጡና ልዑል እግዚአብሔር ዘራቸውን እንደ ሰማይ ከዋክብት ፤ እንደ ባሕር አሸዋ ያብዛልን በማለት ቡራኬ ሰጥተው አሳርገው ሠርሆተ ሕዝብ ተደረገ ።

ወዲያው ለተሰበሰቡት ለብፁዓን ጳጳሳት ፤ ለልዑላን መሳፍንት ፤ ለክቡራን መኳንንት ፤ ሚኒስትሮች ፤ ለሊቃውንትና ለካህናት ፤ ለመንግሥት ሠራተኞች ግርማዊት እቴጌ ሰፊ ግብዣ አደረጉ ።

አለቃ አፈ ወርቅ ዘውዴ ስለቅዱስ ጳውሎስ በዓል በሰዋስወ ብርሃን የተቀኙት ቅኔ

### (ሀ) ክብር ይእቲ ።

ፍኖተ እምከ ይኅበር የማናዊ ፍና ኀቦከ እግዚእ ።
ደወለ ዐይነ ከርም ሖረ እምሑረትከሰ ከልእ ።
ሑረተ ኬፋ ወሳውል በፍኖትከ ርቱዕ ።
እስመ እንዘ ዋሕድ በሥርው ኢየኀብሩ ማዕረረ እክል ወዘርዕ ።

### (ለ) ዕዝል ዕጣነ ሙጋር ።

በዓለ እለ ሳውል ረብሐ በአርጎዎ ክረምት ኑሚኦ ።
ኃምስ እሥራ ኃምስ ለአይድዮ ።
ርኅወ ሰማይ ወረብሐ ወርቅ ፤ ወለተ ጊዮርጊስ ትስዎዮ ።
ለኃይለ ሥላሴሰ ይጼውዮ ።
ወይብሉ ቃልከ መዐዛ ለቤተ በዓል ይምልዮ ።
በዕልፍ ወበአዕላፍ ተመየጥ እግዚኦ ።
እስመ ለርትዑቃን ሰላም ወዳኅና ለቅሩባኒሁ ገቢኦ ።
ኃይለ ሥላሴ ፍቅርነ ዘርኅቀተ ሀገር ኢክልዮ ።
ወለተከፍሎቱ በተጋብዮ ።
ዘሊቀ ጳጳሳት ባስልዮስ ኢነኀጥኦ ።
ኅበ ሀሎ መዝገቡ ተበፅዮ ።

### (ሐ) መወድስ ።

ኃይለ ሥላሴ መዝገብ ዘኢትቀብል ፤ እምቱሳሕ ሰሎሞን ኪን ፤ ወዕቁረ ኢዮብ ትዕግሥት ።
ጣዕመ ንግሥከ መዓር ጽጌ ባስልዮስ ክህነት ።
ወትጠበብ በይነ ጣዕሙ ፤ ዘረትዐ ላቲ ላዕላዊ ፍኖት ።

www.ethiopianortodox.org

ወለተ ጊዮርጊስ ንፅሕ ዚአከ ፤ እስመ በጳውሊ ወጴጥሮስ መሥገርተ ፀርከሙ ተቀጥቀጠት ።
ተዐይልሂ ገዳማቲ በአክናፊ ጸጋ ወሀብት ።
ታስተጋብኦሙ ለንጹሐን ደጌያቲ ገዳም መነኰሳት ።
መለተ ጊዮርጊስ ንሀብክ ንሀበ አስኔት ።
ቤተ ክርስቲያን በምግባሪሃ አምጣነ ይእቲ ማኅቶት ።
ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ በዓል በተከበረበት ሐምሌ ፭ ቀን የዕውራን እስተማሪ የሆነው አቶ ማቴዎስ ደምሴ ያደረገው ንግግር ።

## ግርማዊት ሆይ ።

እኔ እንስቴ የሆንኩ ድኃዎ ዛሬ በዓይነ ሥውሮች ስም ሆኜ በፊትዎ ቆሜ ስናገር ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነው ።

## ግርማዊት ሆይ ።

አባት እናት የሌላቸውን ድኆችን በልዩ ገንዘብዎ ለመርዳት ሲሉ አሁን ያለን በትን ት/ቤት ስላቋቋሙ ብዙ ተማሪዎች በዘመናዊ ጥበብ ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ወገኖቻቸውን ጭምር ረድተው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ማሰብ የዘወትር ተግባርዎ ስለሆነ በየጊዜው ሰፊ ልግሥናዎን አያቋርጡም ።

ስለዚህ ት/ቤቱ ፍሬውን በየጊዜው አፍርቶ ለመመዝገብ የተዘጋጀ ነው ።

ሁለተኛ ቀጨኔ ባለው ቦታ እናት አባት የሌላቸውን ሕፃናት ብቻ ሳይሆን ወንዶች ዓይነ ስውሮች የብሬል ትምህርት ተምረው ሴቶች ዓይነ ስውሮች ሳይማሩ ቢቀሩ ጉዳት መሆኑን ግርማዊትነትዎ ስለተረዳው ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ለሴቶች ዓይነ ሥውሮች ት/ ቤት ከፍተው በዘመናዊ ጥበብ እጃቸውን ይዘው ስለሚመሯቸው ታሪክዎ በዓለም ፊት ከፍ ያለ ከመሆኑም በላይ እስከ ዘለዓለም ምስክር ሆኖ ይኖራል ።

በአሜሪካን አገር ሶስት መቶ ስምንት ሺህ ዓይነ ሥውሮች ሲኖሩ እነዚህ ሁሉ በልዩ ልዩ ጥበብ ራሳቸውን ረድተው ደስተኞች ክርስቲያኖች ሆነው ይኖራሉ ። ይኸውም መጀመሪያ ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ የቻሉት እንደግርማዊና እንደግርማዊት በመሳሰሉ ክርስቲያኖች ርዳታ በቆሙ ት/ቤቶች ነው ።

አሁንም የግርማዊነታቸው ወደ አሜሪካ መሔድ ለሀገራቸው ልማትና ለሕዝባቸው ዕድገት ስለሆነ ፤ ለኢትዮጵያ ዓይነ ሥውሮች የበለጠ ይዘውልን እንዲመጡ ሙሉ ተስፋ አለን ።

## ግርማዊት ሆይ ።

በብፁዕ አባታችን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድ ፤ ብፁዕ አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ ዓይነ ሥውሮችን እንዳስተምር በየካቲት ወር ፲፱፻፵፯ ዓ ም ወደዚህ ት/ቤት



ስለላኩኝ በት/ቤቱ የሚገኙት ዓይነ ስውሮች አማርኛ ንባብና ጽሕፈት በአጭር ጊዜ ችለዋል ።

ዕድሜ ለግርማዊና ለግርማዊት ።
" ለልዑላን ቤተ ሰቦቻቸው ።
ኢትዮጵያ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር ።
አሜን ።

## ፲፱፻፵፯ ዓ፡ ም፡ ሐምሌ ፯ ቀን የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ በዓል አከባበር ።

ሐምሌ ፯ ቀን የአጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበረ ፤ ሐምሌ ፯ ቀን በ፯ ሰዓት ስለ ሥርዓተ ዋዜማው የደወል ድምፅ በተሰማ ጊዜ የደብሩ መዘምራንና ከየሌሎቹም አድባራት ብዙ ሊቃውንትና መዘምራን ሥርዓተ ዋዜማውን ለማድረስ ተሰብስበው የዋዜማውን ቁመት በጀመሩ ጊዜ ፤ የካህናቱ ብዛት በጣም ያስደንቅ ነበር ።

ሥርዓተ ዋዜማውም ተጀመረና ነአምን ወናመልክ የሚለው ዋዜማ ከደረሰ በኋላ ፤ መሪው ቀኝጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ከዚህ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

## ዋዜማ ቅኔ ።

በምሥየጠ አብርሃም ቀዳማዊ ፤ አጋእዝተ ሰማይ ተረክቡ እንዘ ይሣየጡ ሕቀ ።
አግብርት እሙተሣየጡ ብሩረ ወወርቀ ።
እም እመ ነዌ ወኪራም እመ ዘበምድር ሐልቀ ።
ዘበውስተ ሰማይ ይርአይ አብርሃም ጽሕቀ ።
ወአቅረበ ሰማየ ዘርኅቀ ።

ሁለተኛው ዋዜማ ቅኔ ለሐር አምባ ሚካኤል ደብር አስተዳዳሪ ለአለቃ እምኃ ስለ ተሰጠ ፤ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

## ዋዜማ ቅኔ ።

አብርሃም ይቤሎሙ ፤ ለመንክራቲሁ አኃው እለ እጽንዑ መቅደሰ ።
ሰብሕዎ ለስመ ሥላሴ ስብሐተ ሐዲሰ ።
እስመ ላህመ አብርሃም አብ ፍና ቤተ ኤልያስ ጌሠ ።
ወገደፈ ድኅረ ብሉየ ልብሰ ።
ተአፂፎ ልብሰ ባዕር ማዕሰ ።

ሦስተኛው ዋዜማ ቅኔ ለአለቃ አሥራት ስለተሰጠ ፤ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

## ዋዜማ ቅኔ ።

በእሳት ተዋንዮቱ ፤ ለወልደ ገሞራ መዓት እስመ እም ንዕሱ ወዓቅሙ ።
አልሐቅዎ ኃጣውእ ፍዳ አቡሁ ወእሙ ።

www.ethiopianortodox.org

እንበለ ንስሓ ተግሣፅ ተረፈ ላህመ አብ ሊቆሙ ።
ወለወልደ ቢሁ ሰናዖር ጥቀ ደሙ ።
ኢተረክበ ፍና ዳታን አፅሙ ።

አራተኛ ሥላሴ ቅኔ ለአዲስ ዓላም ደብረ ጽዮን የሐዲስ መምህር ለአለቃ አፈ ወርቅ ስለተሰጠ የሚከተለውን ተቀኙ ።

ሥላሴ ቅኔ ።

ቅድሳት ዘቀዳሚ ፤ ወደኃራዊ ትንሣኤ ሥጋ እለ ኅቡራን ልሕቁ ሐመልማላተ ወሣዕረ ።
ይሴሰይ ላህመ ከለዳዊ አብርሃም ወፈረ ።
ውስተ ተአንግዶ ምግበሙ ሥላሴ ዘረሰይዎ ምሕዋረ ።
ወላህመ አብርሃም ኢኀደረ ።
ውስተ ኀለ አቤል ሞት አኮኑ መተረ ።
ከይፈ እዱ ለአብራም ማዕመረ ።

ከዚህ በኋላ ሰላም ተጸፋና የሥርዓተ ዋዜማው ፍጻሜ ሆነ ።

## የዕለተ በዓሉ አከባበር ።

ሐምሌ ፯ ቀን ረቡዕ ከሌሊቱ ፯ ሰዓት ሲሆን ተደወለና የየአድባራቱ አለቆችና መዘምራን እንዲሁም የደብሩ መዘምራን ተሰብስበው ሥርዓተ ማኅሌቱ በሚገባ ሆኖ ሲከናወን አደረ ።

ሥነ ማኅሌቱም ስብሐተ መላእክትን መስሎ በሚያስደንቅ ላህይ በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በመዘምራኑ ፊት ለፊት ባለው ደረጃ ክፍ ባለ ወንበር ሆነው ሲመለከቱ ከማኅሌቱ ጣዕም የተነሣ ፊታቸው በደስታ ብርሃን ተሸልሞ ይታይ ነበር ።

ማኅሌቱም በመልክም ተከናውኖ ከተመለጠነ በኋላ ይትፌሣሕ ልሳንየ በጽድቀ ዚአከ እግዚኦ በሚል መነሻ የሚጀምረውን መዝሙረ ክሥተት መዘምራኑ ግራና ቀኝ እየተቀባበሉ ሲያደርሱት በጣም አስደሰተ ። ቀጥሎም ሚበዝኁ ቅኔ የመሪው የቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ ስለ ነበረ የሚከተለውን ተቀኙ ።

ሚበዝኁ ቅኔ ።

አበ ብዙኃን አብርሃም በበሕቅ ዘዐርገ ኀበ ሠለስቱ አዕፁቀ ።
ፍሬ ጽድቅ ብዙኃ አውረደ ለደቂቀ ።
ሕመ ዘመንግሥት ጽልበ ዘርኅበ እምሕዝበ ዓረብ ወሠርቀ ።

ይህን ከተቀኙ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ፤ ብፁዓን ጳጳሳት፤ ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ባሉበት ታቦት ወጥቶ ዑደት በተደረገ ጊዜ አቀድም አእኰቶቶ ለእግዚአብሔር ብለው መዘምራኑ አሸብሸበው ወዲያው ምህላ ደረሰና ታቦት ገብቶ ሥርዓተ ቅዳሴው ተጀምሮ በመልክም ቅልጥፍና ተፈጸመ ።



በዚሁ ቀን መሪው ቀኝ ጌታ ወልደ ጊዮርጊስ የተቀኙት

ክብር ይእቲ ።

እመ ዕለተ ዓርብ ተገብረ ዘኢተገብረ በኀበ አሕዛብ ወሕዝብ ።
እስመ ዘኢተአንመ ልብስ እንዘ ይትረከብ በዓርብ ።
ሰማይ ተአርቀ እምኒ ልብሱ ከከብ ።
እንከሰ ይኀድጉ ፤ ሕዝበ ቀያፋ በዊአ አሐቲ ምሥራብ ።

ዕጣነ ሙጋር ።

መሥፈርተ አብርሃም ኄር እመ ታገምር ሠለስተ ።
አጋእዝቲሁ ኢገብረ አርባዕተ ።
ላዕለ ሠለስቱ አጋእዝቲሁ እስመ ኢወሰከ ምንተ ።
ብዙኀነ አማልክተ ።
ዳዕሙ ያሰስል እምድሩ ዘሰባልዮስ ሐሰተ ።
ጸውዓ ውስተ ጉባኤሁ ሥላሴ ሰማዕተ ።

እሠረ ንጉሥ ።

ኃይለ ሥላሴ መጠነ ወአእመረ ምድረ እስራኤል ስፍሕተ ።
አኮኑ ኄራን ሥላሴ ተናገርዎ ጽሚተ
ኢልያስሂ በዘተከብተ ።
ያስተራትዕ ለነ ኵሉ ፍኖተ ።
ይትኀፈሩ ዘኮኑ ዕቅፍተ ።

እንዲህ ሁኖ ሥነ በዓሉ በግሩም ሁናቴ ከተፈጸመ በኋላ ፤ የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ አስተዳዳሪና የብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በቤተ ክርስቲያኒ ሲያገለግሉ ለዋሉት አለቆችና መዘምራን ለዚሁ አስበው ባዘጋጁት ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ታላቅ ግብዣ አድርገውላቸዋል ።

በማግሥቱም ሐምሌ ፰ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓ ም ከምሽቱ ሩብ ሰዓት ጀምሮ ብፁዕነታቸው በዚሁ አዳራሽ ተገኝተው ለቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትና ለቤተ ክህነት ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት ሹማምንትና ሠራተኞች እንዲሁም ለመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ደስ የሚያሰኝ የራት ግብዣ አድርገዋል ።

በግብዣውም ጊዜ ይጐርፉ የነበሩት የደስታ መግለጫ ቅኔዎች በጣም ደስ የሚያሰኙ ነበሩ ።

ይልቁንም ሊቀ መዘምራን እነሊሉ ገብረ ኪሮስ ብፁዕነታቸው በመንፈሳዊውና በሥጋዊው አስተዳደር ያለባቸውን ሰፊ ድካምና ቅን አስተያየት በመዘርዘር ሰፊ የሆነ የቃል ንግግር አድርገው ከሌሊቱ በአራት ሰዓት የግብዣው ፍጻሜ ሆኗል ።

## የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ስብሰባ ከግንቦት ፲፩ ቀን እስከ ሰኔ ፲፱ ቀን ።

ብፁዓን ጳጳሳት ከየሀገረ ስብከታቸው፤ ክቡራን ሊቃውንት ከየአድባራቱ፤ ክቡራን መምህራን ከየገዳማቱና ከሚያስተምሩበት ቦታ እየተሰበሰቡ በየዓመቱ በርክበ ካህናት

www.ethiopianortodox.org

ዕለት ስለቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ሥነ ሥርዓት የምክር መሻሻል ሲያደርጉ ስድስት ዓመት ሆኗቸዋል ።

እነሱን አሟሥቶ ወደ ኀብረታዊ ተግባር የመራ ፈቃደ እግዚአብሔር በሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ትእዛዝ በየጠቅላይ ግዛቱ ያሉትን የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆች አስተባብሮ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የምትስፋፋበትንና የስብከት ብርሃን በሰፊው የሚዘረጋበትን አቅድ ስለ አሳሰባቸው ከፍ ያለ አስተያየት ሰጥቱዋል ።

በእውነቱ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ መሆን የእግዚአብሔር አደራ ጠባቂ መሆን ስለሆነ ፤ የታዘዘውን ማጉደል ይቅርና ከታዘዘው አትርፎ መሥራት እንደሚገባን ከወቅን ፤ የሥጋንና የነፍስን በረከት የምናገኝበትን ሥራ ሠርተን በሁለት ዓለም መጠቀም እንችላለን ።

ይኸውም የሚገለጠው በወዲህ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳቱ በጎ ሥራችንን ተመልክተው በጸሎታቸው በቡራኬያቸው ይባርኩናል ፤ ንጉሠ ነገሥቱም ተደስተውብ ልግስናቸው ይጉበኙናል ።

በወዲያውም ልዑል እግዚአብሔር አደራውን አክብረን መጠበቃችንን ተመልክቶ ፍጻሜ የሌለው ክብርን ይሰጠናል ።

ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ መተባበርና ያንድነት ድካም ማድረግ ይህን የመሰለውን ዘለዓለማዊ በረከት የሚያስገኝ በመሆኑ ፤ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ሠራተኞች ሥርዓተ ምክር በሚቀጥሉት መሥመሮች ስንገልጥ ሕለናችንን ደስታ ይሰማዋል ።

ጉባዔው የስብሰባ ሥራውን በጀመረበት ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በመሰብሰቢያው አዳራሽ ተገኝተው ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ፤ ስለጉባኤው ሥራ መክፈቻ ፤ ጠቃሚ የሆነ ንግግር አድርገዋል ።

ከብፁዕነታቸው ንግግር በፊት ፤ የጉባኤውን ሥራ ሲያከናውኑ የሰነበቱት የዓቢይ ጽ / ቤት (የቤተ ክህነት ጠ ጽ ቤት) ሹማምንቶችና የየጠቅላይ ግዛቱ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆች ስም ይቀጥላል ።

የ ቤ ተ ክ ህ ነ ት ጠ ቅ ላ ይ ጽ| ቤ ት ።

| ተራ ቁ | ስም | የማዕርግና የሥራ ክፍል ። | |
|---|---|---|---|
| ፩ | አቶ አበራ ዠምበሬ | የቤተ ክህነት ጠ ጽ\| ቤትዋና ጸሐፊ | ሰብሳቢ |
| ፪ | አለቃ ልሳነ ወርቅ ወልደ ዳዊት | ,, ,, ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት | አባል |
| ፫ | አፈንጉሥ ደምሴ ማህሌ | መጋቤ ክህናት | ,, |
| ፬ | አቶ አስፋው ደምስ | ,, ሀብታት | ,, |
| ፭ | ,, ኃይሌ ወልደ መድኅን | የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሹም | ,, |
| ፮ | ,, ተክለ ጊዮርጊስ ዕቁበ እግዚእ | መጋቤ ሒተታ | ,, |
| ፯ | ,, ጸጋየ ወልደ ሰማዕት | በመጋቤ ክህናት የሠራተኛ አ\| ክ\| ሹም | ,, |
| ፰ | ,, በትረ ገብረ መድኅን | በመጋቤ ሀብታት የሂሣብ ሹም | ,, |
| ፱ | ,, አስፋው ተክሌ | [illegible] | ,, |
| ፲ | ,, ገብረ ሥላሴ ጥበቡ | ከመጋቤ መዝገብ ቤት ክፍል | ,, |
| ፲፩ | ,, ጌታሁን ገብረ ወልዱ | የመልክት ክፍል ሹም | ,, |
| ፲፪ | ,, ኪዳነ ወልድ | የመዝገብ ቤት ,, | ,, |
| | ለ የ ጠ ቅ ላ ይ ግ ዛ ቱ ቤ ተ ክ ህ ነ ት ጽ\| ቤ ት ። | | |
| ፲፫ | አጋፋሪ በየነ ዓሊ | የሸዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ | አባል |
| ፲፬ | መምህር በኩረ ጽዮን | የወሎ ,, ,, ,, | ,, |
| ፲፭ | አባ ዘካርያስ | የሐረር ,, ,, ,, | ,, |
| ፲፮ | አቶ ደምሴ አበባው | የትግሬ ,, ዋና ጸሐፊ | ,, |
| ፲፯ | መምህር በላይ መርሻ | የጐንደር ,, ሥራ መሪ | ,, |
| ፲፰ | ,, ምትኬ ይመር | የጐጃም ,, ,, ,, | ,, |
| ፲፱ | አባ ተክለ ሃይማኖት ካሣ | የወለጋ ,, ,, ,, | ,, |
| ፳ | ሊቀ ካህናት ስንቄ ዱባለ | የአሩሲ ,, ,, ,, | ,, |
| ፳፩ | አቶ በለጠ ላይ ገፋ | የኢሉባቦር ,, ,, ,, | ,, |
| ፳፪ | መምሬ እንደሻው ወሰኔ | የከፋ ,, ዋና ጸሐፊ | ,, |

ከዚህ በቀር የየጠቅላይ ግዛቱ ሂሣብ ሹሞች ከገሙ ጐፋና ከሲዳሞ በቀር በስብሰባው ላይ በሙሉ ነበሩ ።

## በመጀመሪያው ስብሰባ ዋናው እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ስለ ጉባኤው ሥራ መክፈቻ የተናገሩት ቃል ።

እንድትሰበሰቡ ያደረግንበት ምክንያት ተሰብስቦ መነጋገርና መመካከር የሥራ አካልንም መግለጽ ብዙ ጥቅምን የሚያስገኝ መሆኑንና ፤ በመገባባት አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥም ብዙ የሥራ መሻሻል ዘዴ ሊገኝ የሚቻል መሆኑን በማመን ነው ።

www.ethiopianortodox.org

ይህንም ዓይነት ስብሰባ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑ ታውቆ ፤ በአገር ግዛትም ሆነ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ፤ በሌሎችም መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ፤ ሲሠራበት ይታያል ። እኛም ከጥንት ከአበው ተያይዞ በመጣው ረከበ ካህናት በተባለው በዛሬው በዓላችን የሰበሰብናችሁ በዚሁ ምክንያት ነው ። ስለዚህ ፤ በየክፍል መሥሪያ ቤታችሁ የገጠማችሁን ችግር በጽሑፍም በቃልም ገልጻችሁ እንዲቃለልላችሁ እንድታደርጉ እናሳስባለን ። ልዑል እግዚአብሔር የተሰበሰባችሁበትን ሥራ ያቃናላችሁ ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ ።

ቀጥሎም ፤ ዋና ጸሐፊው አቶ አበራ ዠንበሬ የስብሰባውን ምክንያት በመዘርዘር የሚከተለውን አጭር ንግግር አደረጉ ።

በማናቸውም አገርና መሥሪያ ቤት ፤ ሹማምንቱ በተወሰነ ጊዜ እየተሰበሰቡ ለሥራቸው መልካም እርምጃ መመካከራቸው የታወቀና ከፍ ያለ ጥቅም ያስገኘ ልማድ ነው ። በዚሁ መሠረት የቤተ ክህነት የመሰብሰቢያ ዕለት በሆነው ረከበ ክህናት በተባለው በዛሬው በዓላችን ቀን የመጀመሪያ ጠቅላላ ሰብሰባ አድርገናል ። የዚህም ስብሰባ ጥቅሙ አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥና የጋራ ችግርን በመወያየት ፤ ለችግሩ ማቃለያ የሆነ ዘዴን አግኝቶ ለወደፊት በተሻለና በበለጠ ሁኔታ የክፍል ሥራን ለማከናወን ነው ።

ከአንድ ወይም ፤ ከሁለት ሰው አሳብና አቅድ የብዙዎች አሳብ የተሻለ ፍጻሜ እንዲያገኝ የታመነ ነው ። በዚህም መንፈስ ስለ ቤተ ክህነት ሥራ መቃናት እንድንመካከር ጥሪ አድርገንላችሁ እነሆ ከተጠራችሁት ሹማምንት ብዙዎቹ በመካከላችን ስለ ተገኛችሁ በጣም ደስ ብሎናል ።

የጋራ ዓላማችንን በኅብረትና በመግባባት እንድንመሠርት ተስፋ የጣልንበትን ሥራችንንና አሳባችንን የተባረከና የተቀደሰ ያደርግልን ዘንድ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ልመናዬን አቀርባለሁ ብለው ከተናገሩ በኋላ ፤ ለሥራው አመራር ያዘጋጁትን ሥርዓተ ጉባኤና የሥራ ማመልከቻ ፤ የአቀራረቡን ተራ የሚገልጽ ፕሮግራም አስመጥተው ለአባሎቹ በሙሉ እንዲታደል ተደርጎ ፤ የሐረር ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ አባ ዘካርያስ አሳርገው ጉባኤው ለግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ ም ተቀጠረ ።

<u>የጉባኤው ተራ ፕሮግራም ።</u>

ግንቦት ፲፩ ረቡዕ ጥዋት የጉባኤው መክፈቻ ።
" ፲፪ ሐሙስ ትግሬና መጋቤ ሐተታ ።
" ፲፫ ዐርብ በጌምድርና መጋቤ ሀብታት
ከእኩለ ቀን በኋላ ወሎ ።
" ፲፬ ቀዳሚት ጥዋት ጐጃምና መጋቤ ካህናት ።
" ፲፮ ሰኞ ጧት ወለጋና ዐቢይ ጽሕፈት ቤት ።
" ፲፯ ማክሰኞ ሸዋና ሊቀ መጣኒ ፤



ከእኩለቀን በኋላ ፤ ሐረርና መጋቤ መንክሳት ።
ግንቦት ፲፰ ረቡዕ ጥዋት አሩሲና ማተሚያ ቤት
ከእኩለቀን በኋላ ሲዳሞና ገሙጎፋ ።
" ፲፱ ሐሙስ ጥዋት የትምህርት ቤቶችና ከፋ ።
" ፳ ዓርብ የገንዘብና የንብረት ኮሚቴ ።
ከእኩለቀን በኋላ የአስተዳደር ።
" ፳፩ ቅዳሜ ጥዋት የሒሳብ አያያዝ ስብሰባ ።

<u>ሥርዓተ ጉባኤ ።</u>

አባሎቹ በሙሉ በተወሰነው ሰዓት ከወንበራቸው ላይ መገኘት አለባቸው ። በየዕለቱ ከስብሰባው መክፈቻና መዝጊያ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ጸሎት ስለሚደረግ ሁሉም ቆመው አንቃዕድዎ ማድረግና በጸሎት ተካፋይ መሆን ይገባቸዋል ።

ጉባኤው ከተጀመረ በኋላ ማንኛውም አባል ያለ ፈቃድ ከስብሰባው ላይ ተነሥቶ መሔድ አይፈቀድለትም ።

ሰብሳቢው ለአባሎቹ የሚገልጸው ማስታወቂያ ቢኖር ፤ ተናግሮ ስብሰባው አሁን በደንቡ መሠረት ተከፍቷል ካለ በኋላ የጉባኤው ሥራ ይጀመራል ።

የሥራም መጀመሪያ ሆኖ ያለፈው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ተነበ ይጸድቃል ፤ ወይም ይሻሻላል ፤ የሚጸድቅም ሲሆን ከየሀገረስብከቱ የተላኩት ዋናመልክተኞችና የጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ የክፍል ሹማምንት ይፈርሙበታል ።

ከዚህ በኋላ የዕለቱ ሥራ እንደ ቅደም ተከተልነቱ ይቀጥላል ።

የሚቀርበውን የሥራ መግለጫ አቅራቢው ለማንበቢያ በተሰናዳው ሥፍራ ቆሞ ከፍ ባለ ድምጽ ያነባል ፤ ራፖሩ በሚነበብበት ጊዜ ሌሎቹ አባሎች የሚጠይቁት ወይም ሊከራከሩበት ያሰቡት ነገር ቢኖር በማስታወሻ ይዘው ንባቡ ካለቀ በኋላ ይጠይቃሉ እንጂ ንባቡን ማደናቀፍ አይፈቀድም ።

ንባቡ ሲፈጸም ፤ አቅራቢው ለማንበቢያ በተዘጋጀው ሥፍራ ተቀምጠ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ መስጠት አለበት ፤ በዚህ ጊዜ የሒሳቡ ሠራተኛ ወይም ረዳቱ ሊረዳው ይችላል ።

በጥያቄና መልስ ፤ የቀረበው ራፖር ለሁሉም ግልጽ ከሆነ በኋላ ፤ ስለ ቀረቡት አሳቦች አንድ ባንድ የአሳብ መለዋወጥ ይደረጋል ።
የቀረበው አሳብ ጥቅምና ጉዳት ተገልጦ ከታወቀ በኋላ ይህ አሳብ በእንዲህ ያለ ሁኔታ እንዲወሰን አሳስባለሁ ሲል ከአባሎቹ አንዱ የአሳብ አንቀሳቃሽ ሲሆንና ሌላው ሲደግፈው በጉዳዩ በሰፊው ንግግር ይደረግበታል ።

ክርክር በሚደርግበት ጊዜ የጉባኤው አባል አንዱ ወይም ብዙዎቹ ከጉዳዩ ምሥመር የወጡ እንደሆነ ከአባሎቹ አንዱ ቀኝ እጁን ብቅ (ከፍ) አድርጎ ስለሥነ

www.ethiopianortodox.org

ሥርዓት ለማስታወስ ይፈቀድልኝ ብሎ ፈቃድ ከጠየቀና ለመፈቀዱ ከስብሰባው መልስ ካገኘ በኋላ ክርክሩ ከመሥመሩ መውጣቱን ለማስረዳት ይችላል ።

እንደዚሁም ሰብሳቢው ክርክሩ ከመሥመሩ መውጣቱ በተሰማው ጊዜ ክርክሩ ወደ ሥረ ነገሩ እንዲመለስ ያደርጋል ።

የቀረበውን፡አሳብ ከአባሎቹ አንዱ የተቃወመና ሌላውም የደገፈው እንደሆነ ፤ አባሎች ድምጽ እንዲሰጡ ተጠይቀው ጉዳዩ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል ።

የአባሎቹ ድምጽ እኩል በእኩል ሆኖ ከሁለት የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወዳለበት ወገን ይጸናል ።

## የስንብት ጊዜ ።

የጉባኤው ሥራ ከተያያዘ ቀላይ እንደተፈጸመው [illegible] በጉባኤው ላይ መንፈሳዊ ፤ በሚገባ [illegible] ከስገኘ በኋላ ፤ በጉባኤው ፤ ለነበሩትና ለየጠቅላይ ግዛቱ ሥራ [illegible] ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት [illegible] ታዘዘላቸውና የግብዣው ሥርዓት ሰኔ ፮ ቀን በዕለተ ጳራቅሊጦስ በዋናው ጸሐፊ በአቶ አበራ ዡንበሬና በአቶ ተክለ ሚካኤል ተክለ ወልድ አስተናባሪነት ተከናወነ ።

በግብዣው ጊዜም ፤ የካህናት አስተዳዳሪ (መጋቤ ካህናት) አጋፋሪ ጅምሬ [illegible] የቤተ ክህነት መጋቤ ሀብታት አቶ አስፋው [illegible] የአስተናባሪነቱን ሥራ [illegible] ሥን ሥርዓት ሲጠባበቁት ያስደስቱ ነበር ።

ተጋባዦቹም በንጊት ሃይማኖት ወንድማማቾች የሆኑና በንጊት መንፈስ ማዕድ የተሳተፉ እንግዶች መሆናቸው ፤ የጭውውታቸው ጣዕም የተመለከትን ልብ የሚማርክ ነበር ፤ የግብዣውም ሥርዓት ሲፈጸም የጉጃም ሊቀ ካህናት አባ ምትኬ [illegible] ገው አሳረጉና ወደየቤታቸው ሔዱ ።

ከዚህ በኋላ ፤ ወደብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት መንበር ፊት ቀርበው በስብሰባቸው ያጠኑትን የወደፊት አቅዳቸውን የሚናገሩበትና ከብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ቡራኬን የተመላ ስንብት የሚቀበሉት ጊዜ ስለተቃረበ ፤ በዋናው ጸሐፊ በአቶ አበራ ዡንበሬ አመልካችነት እንዲቀርቡ ከብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድ ተሰጠ ።

ወደ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት እንዲቀርቡ የተፈቀደላቸው ቀን ሰኔ ፲፱ ከ፲፭ ሰዓት ጀምሮ ስለነበረ ፤ በዚሁ ቀን በዘጠኝ ሰዓት ስብሰባ ተደርጎ ያቀረቧቸው ንግግሮች መልእክት ሆኖ ከተሰናዳ በኋላ ፤ ከአሥራ አንድ ሰዓት ወደ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ፊት ቀርበው ቅዱስ መስቀልን እየተሳለሙ ሥፍራ ሥፍራቸውን ከመጋቤ ካህናት አጋፋሪ ጅምሬ ተቀብለው በዋናው ጸሐፊ በአቶ አበራ ዡንበሬ አስተናባሪነት ተረዳደው ቆመው ጊዜ ፤ ስለጠቅላላው ሥራ አካሔድ ዋናው ጸሐፊ የሚከተለውን የአሳብ መግለጫ ንግግር ።



## የዋናው ጸሐፊ ንግግር ።

ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ፤

በጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ በተደረገው የመጀመሪያ ጠቅላላ ስብሰባ ተካፋይ የሆኑት ፤ የየሀገረ ስብከቱ የሥራ አስኪያጆች ፤ ዋና ጸሐፊዎችና የሒሳብ ሠራተኞች እንዲሁም የጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱና የቤተ ክህነት ትምሕርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት የክፍል ሹማምንት የተሰበሰቡበትን ሥራ ስለፈጸሙ ፤ ቡራኬ ይቀበሉ ዘንድ ከብፁዕነትዎ መንበር ፊት አቅርቤያቸዋለሁ ።

አሁን ከብፁዕነትዎ መንበር ፊት የቀረቡት ሹማምንት ከግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓ ም ጀምሮ እስከ ዛሬ በየዕለቱ እየተሰበሰቡ ስለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ፤ ስለ ሥራችን መቃናትና መከናወን ከየክፍሉ በቀረቡት የሥራ መግለጫዎችና አሳቦች መሠረት በሰፊው በመነጋገር ከአንድ ወር የበለጠ ጊዜ በመግባባትና በትጋት ከፍ ያለ ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ ሰንብተዋል ።

የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በመካከላችን ተገኝተው ፤ የመጀመሪያውን ጠቅላላ ስብሰባ ሲከፍቱ ተሰብስቦ በመነጋገርና በመመካከር ፤ በመግባባትና አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥ ብዙ የሥራ መሻሻያ ዘዴ ማግኘት ስለሚቻል ፤ ከጥንት ከአበው ሲያያዝ በመጣው በዛሬው በዓላችን የሰበሰብናችሁ በየክፍል መሥሪያ ቤታችሁ የገጠማችሁን ችግር በጽሑፍም በቃልም ገልጻችሁ ችግራችሁ እንዲቃለል እንድታደርጉ ስለሆነ ፤ ልዑል እግዚአብሔር የተሰበሰባችሁበትን ሥራ ያቃናላችሁ ብለው በተናገሩት መሠረት የጉባኤው አባሎች በመግባባት ሠርተዋል ።

በአሁኑም ስብሰባ ለወደፊቱ ሥራ መከናወን የሚጠቅሙ ብዙ ጉዳዮች ተወስነዋል ። አሁን በመግባባት በተወሰነው አሳብ መሠረት ለወደፊት ሥራችንን በተሻለ ሁኔታ ለማራመድ እንደምንችል ሙሉ ተስፋ አለን ።

ከመንበረ ሊቀ ጳጳሳት የቀረቡትና ሌሎቹም የሥራ ጓደኞቼ ለወደፊቱ የበለጠ እንደሚሠሩ ተስፋ በማድረግ አሁን በኅብረትና በመግባባት ስለፈጸሙት ሥራ ከብፁዕነትዎ ፊት ሳላመስግናቸው አላልፍም ።

እንዲሁም በዚህ ዕለት ከብፁዕነትዎ ፊት ቀርበው ለመናገር ዕድል የተሰጣቸው የትግሬ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊ ጉባኤው ስለፈጸማቸው ሥራዎች በሥራ ጓደኞቻቸው ስም ሆነው ንግግር ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው በትሕትና እለምናለሁ ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሳቢነትና ትጋት ፤ በብፁዕነትዎ ተራዳኢነት ራሷን የቻለችው ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው እያደገች እንድትሔድ በፍጹም መንፈስ የምንሠራ መሆናችንንም በራሴና በሥራ ጓደኞቼ ስም ሆኜ አረጋግጣለሁ ።

www.ethiopianortodox.org

ቸሩ አምላክ ብፁዕነትዎን ፤ ብፁዕ ዋናውን እንደራሴና የቀሩትንም ብፁዓን ጳጳሳት በጠቅላላውም በእግዚአብሔር አባትነት የሚያምኑትን በሰውም ልጅ ወንድማማችነት የሚኖሩትን ሁሉ ይጠብቅልን ፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንንም ያደርጅልን ።

የቤተ ክርስቲያናችን አሳቢ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከሔዱበት አገር በሰላም ይመልስልን ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ።
" ለንጉሣዊ ቤተ ሰብ ።
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ፣ ትኑር ።

ከዚህም ቀጥሎ ከየጠቅላይ ግዛቶቹ በመጡት ሥራ አስኪያጆች ስም ሆነው የትግሬ ጠቅላይ ግዛት ቤተ ክህነት ዋና ጸሐፊ አቶ ደምሴ አበባው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

## ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ሆይ ።

የየክፍል ሥራ ውጤታችንን እናቀርብ ዘንድ ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከየ ሀገረ ስብከቱ ተጠርተን የመጣን ታዛዦችዎ ከግንቦት ፲፩ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ባሉት ፴፩ ቀኖች የመጣንበትን የሥራ ጉዳይ ስንመከከር ሰንብተን አሁን ወደየክፍል ሥራችን የምንመለስ ስለሆነ ፤ ቡራኬዎን ለመቀበል ከመንበረ ጵጵስናዎ ፊት እነሆ ቀርበናል ።

በተለይም እኔ ዝቅተኛ ታዛዥዎ በሥራ ጓደኞቼ ስም ሆኜ ስንመከከርበት ስለ ቆየነው ጉዳይ ከብዙ በጥቂቱ ከብፁዕነትዎ መንበር ስር ቀርቤ ለመናገር ዕድል በማግኘቴ ደስታ ተሰምቶኛል ።

## ብ ፁ ዕ ሆ ይ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይግባውና ፤ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰ ቍጥር ፳ እንደተጻፈው ሁለት ወይም ሶስት ሆነው ወደተከማቹበት ከዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ እንዳለው ሙሽራው ስለሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥራ እድገት ለመመካከር በተሰበሰብንበት ጠቅላላ ጉባኤያችን ጌታ እንዳልተለየን ሁላችንም እናምናለን ።

የጉባኤያችንም ዓላማ አሳብ ለአሳብ በመለዋወጥ ለመግባባትና የጋራ ችግራችንን ተመካክሮ ለማስወገድ ፤ እንዲሁም ከአንድ የሥራ ገበታ ፤ ንግግር ተካፋይ በመሆን እርስ በርሳችን ከመተዋወቃችን በላይ ፤ ፍቅራችንን ከማጽናት ጋር በኅብረት ስምንወስነው አሳብ መሠረት የሥራ እርምጃችንን ለማሻሻልና ለማቀልጠፍ ነው ።

ስለ ስብሰባው ባጭሩ ከተናገርኩ ዘንድ ጉባኤው ወደፊት ስለአቀዳቸው ዓበይት ሥራዎች ከሙሉ በክፍሉ ለመግለጽ ይፈቀድልኝ ።



## ብ ፁ ዕ ሆ ይ ።

በብፁዕነትዎ መሪነት የምትተዳደረው ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የመሻሻል እርምጃዋ እየተፋጠነ ሔዷል ፤ ብርሃነ ኢትዮጵያ የሆነ ቅድስናዎን የማግኘት ዕድላችንን አቅኚ የሆኑልን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሥርወ መንግሥትነታቸው ለኢትዮጵያ መሪ ከሆኑባት ከታወቀችውና ከተመረጠችው ቀን ጀምሮ ለበጎ ሥራቸው ሁሉ ተቀዳሚ የሚያደርጉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን እድገትና የተዋህዶ ሃይማኖትን መስፋፋት ስለሆነ ፤ እነሆ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ መብት ያላት ለመሆን ቻለች ፤ ይኸንኑም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን የበጎ አድራጎት ድካም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም የማትዘነጋው በመሆኑ ፤ ጥብቅ ምስጋናዋንና ስለጤንነታቸውም ልባዊ ጸሎቷን ከማቅረብ በዝና አታውቅም ፤ ግርማዊነታቸው የሚያደርጉት ልግሥና በየጊዜው እየቀጠለ በመሔዱ ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምድረ ኢትዮጵያ ቃለ ወንጌልን ለመዝራት በትጋት ስትሠራ ትታያለች ፤ እንዲሁም በብፁዕነትዎና በብፁዕነትዎ ዋና እንደራሴ በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በቀሩትም የየሀገረ ስብከቱ ብፁዓን ጳጳሳት ቀን አሳቢነትና መንፈሳዊ መሪነት የቤተ ክህነት የሥራ ክፍሎች እርምጃ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀለጠፈ በመሔዱ ከፍጹምነት የሚደርስበት ጊዜ እሩቅ መስሎ አይታየንም ።

ለሁሉም ጊዜ አለው እንደተባለው ሁሉ ፤ የ፲፬ ጠቅላይ ግዛቶች የቤተ ክህነት ሹማምንት ባሉበት ለለቤተ ክህነት አስተዳደር ለመመካከር የቻልንበት ይህ አጋጣሚ ጊዜና ዕድል የተቀደሰ ነው ።

## ብ ፁ ዕ ሆ ይ ።

ለጉባኤው ቀርበው ከተመከረባቸው ጉዳዮች ውስጥ በተለመደው የብፁዕነትዎ ሥራ ትጋት ተፈጻሚነትን እንዲያገኙ ጉባኤው ያቀረባቸውን አሳቦች በልዩ ማስታወሻ ከዚህ ጋር ለብፁዕነትዎ አቅርበናል ።

፩ኛ/ ከዚህ ጉባኤያችን ላይ ተቀዳሚና የበለጠ አድርገን የተመከከርንበት ስለየኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እየገነነ ስለሚሔድበት ሁኔታና ስለስብከት ሥራ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያናችንን ታሪክና የሥራ ፍሬ ለሕዝብ የሚያዘክር አንድ መንፈሳዊ ቤተ መጻሕፍትና የአንቲክ ቤት አዲስ አበባ ላይ እንዲከፈት ጉባኤው በሰፊው አስበበታል ፤ እንዲሁም በየሀገረ ስብከቱ ያለን የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ዓበይት ሥራችን የሃይማኖት ስብከት ሥራ እንዲስፋ ማድረግ መሆኑን ባለመዘንጋት ችሎታቸውና ሃይማኖታቸው በጉባኤ ተመርምሮ ከየሀገረ ስብከቱ ጳጳሳት በተለይ የተፈቀደላቸው ሰባክያን የስብከት ሥራቸውን እንዲያስፋፉ ለማድረግ አጥብቀን አስበንበታል ፤ ይከውም አሳባችን እንዲፈጸም የብፁዕነትዎ ረድኤት ደጋፊ ይሆነን ዘንድ እንመኛለን ።

www.ethiopianortodox.org

፪ኛ ) የኢትዮጵያን ጥንታዊ ክርስቲያንነትና ልባዊ እምነት በሰፊው በመረዳት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ መሪነት የልዩ ልዩ አህጉር ሕዝቦች በየጊዜው የሚያቀርቡትን ጥያቄ ብዛት በመመልከት ለተፈለግንበት ተግባር ተገቢና ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት ቤተ ክርስቲያናችን ካሏት ሊቃውንት በላይ በተጨማሪ ሌሎች አዋቂዎች መምህራንና ሰባክያን ማሰልጠን የሚገባ በመሆኑ ሐረር ከተማ የልዑል ራስ መኩንን መንፈሳውያን መምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ተብሎ የተሰየመ አንድ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ተቋቁሟል ።

## ብፁዕ ሆይ ።

በጠቅላላው የቤተ ክህነትን ሥነ ሥርዓት በሕብረታዊ መንፈስ ለማቋቋም መሠረት ያደረግነውን የዓቢይ ጉባኤ ሕንፃ ክርሕሰ ማዕዘንቱ አድርሶ እኛም ከአራቱ ማእዘን ጉብኝን ሆነን በዚሁ ሥፍራ የተገኘ ነውን ልዑካን ፈጣሪያችን በሕይወት አቆይቶ ለሚመጣው ዘመን ጉባኤ ያደርሰን ዘንድ እየተመኘን ቅዱስ ቡራኬዎ ይሰጠን ዘንድ ፤ ብፁዕ ቅድስናዎን እንለምናለን ።

ከዚህ በኋላ ፤ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት ስለጉባኤው ሥራ አመራር ቀጥሎ ያለውን ምክር ተናገሩ ።

## - የብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ባስልዮስ ንግግር ።

እናንት ሠራተኞች ፤ ምን ጊዜም ቢሆን መንፈሳዊው ለሥጋዊው የሚተርፈው ስለሆነ ፤ በሥጋዊ በኩል የሚሠራውን ሥራ ስንኳ የሠራተኞች ስብሰባ ሲያሻሽለውና ሲያከናውነው ትመለከቷላችሁ ። ስለዚህ ስብሰባ አድርጎ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ ማከናወን በአባቶቻችን በሐዋርያት ተጀምሮ የተሰጠን ከሆነ ጠቃሚነቱን አውቀን ልንሠራበት ይገባል ።

አሁን ባደረጋችሁት ግንኙነት የሥራ ጓኞቻችሁ አሳብና አሳባችሁ ዕውቀታቸውና ዕውቀታችሁ አብሮ ስለተገናኘ ለአእምሮዋችሁና ለሥራችሁ የበለጠ ብርታትን ይሰጣችኋል ።

ስብሰባችሁም ስለ ሦስት ዓይነት ጉዳይ ነው ፤ ይኸውም አንደኛው ሥራችሁ እስካሁን በምን ሁኔታ እንደነበረ ፤ ሁለተኛው አሁን የሥራችሁ ሁኔታ ምን እንደሆነ ፤ ሦስተኛው ወደፊት ሥራችሁን የምታራምዱት በምን ሁኔታ እንደሚሆን ለመመካከርና አንድነታችሁ በስገኘው ምክር ለመጠቀም ነው ።

ይህንንም በአሁኑ ስብሰባችን ለወደፊት ሥራ መከናወን የሚጠቅሙ ብዙ ጉዳዮች ተወስነዋል ብለህ ስለተናገርከው ሁላችሁ እንደተገነዘባችሁት እረዳዋለሁ ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ሲያስተምር እኔ እውነተኛ የወይን ሐረግ ነኝ ፤ ተክዩም አባቴ ነው ፤ በእኔ ላይ የማያፈራውን ጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል ብሎ የተናገረውን አትዘንጉ ዮሐ ። ም ፲፭ ፤ ቍ ፩



በወይን ጫፍ የተመሰልን ሁላችን ስለሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጐ ፍሬ ምግባርን አፍርተን ለቤተ ክርስቲያናችን እንድናበረክታት ይጠብቀናልና የአንድነት ሥራ መሥራት እንዲገባን በዚህ ምሳሌ ከተረዳን ፤ በቃል ብቻ ሳይሆን በልብም በሥራም በአስተያየትም እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ተዋህደን እንሥራ ። ሆኖም ይህ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት እንደ ሥር እንደ ግንድ ሲሆን ፤ እናንተ እንደ ፍሬው እንደቅጠሉ እንደ ጫፉ መሆናችሁ ነውና የቦታ መራራቅና ለዕለት ሥራ አለመቀራረብ ምንጊዜም አንድነታችሁን ሊለውጥ አይችልም ። አንድነታችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ከጸና ለመንፈሳዊ ክፍል እንደ መመረጣችሁ መጠን ፤ ለሌሎችም መልካም አርአያ እስከመሆን ትደርሳላችሁ ።

ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ጊዜ ያደረጋችሁትን ይህን ስብሰባችሁን ባርኮ በማቴዎስ ወንጌል በኻያ አምስት ምዕራፍ በሐያ አንድ ቁጥር እንደአመሰገነው ሠራተኛ ፤ እውነተኞች የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ተብላችሁ በእግዚአብሔር ቃል ለመመስገን ያብቃችሁ ።

የብፁዕ ሊቀ ጳጳሳቱ ንግግር በተፈጸመ ጊዜ ከብፁዕነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ቀጥሎ የሻይ ግብዣ ከተደረገ በኋላ የስንብቱ ሥርዓት ተፈጸመ ።

---

## ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓም እሑድ

ምስባክ ፤ ወይወስዱ ለንጉሥ ደናግለ ድኅሬሃ ።
ወቢጻሂ ይወስዱ ለከ ።
ወይወስድዎን በትፍሥሕት ወበሐሤት ።
ወንጌል ዮሐንስ ምዕ ፤ ፰ ቍ ፤ ፩-፲፪ ተመልከት ።

## የወንጌሉ ምሥጢር ።

ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያንም ይህቺ ሴት ስታመነዝር አገኘናት ፤ እንደዚችም ያሉ ችሙ በደንጊያ ትወገር ዘንድ ሙሴ በኦሪት አዘዘን ፤ እንግዲህ አንተስ ስለ ርሷ ምን ትላለህ ? ብለው ጌታ ኢየሱስን መጠየቃቸው የሚጣሉበት ምክንያት ያገኙ ዘንድ ሲፈትኑት መሆኑ ተገልጿል ።

ምክንያቱም ትወገር ቢል የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ይላል የሰውጥፋት እያሳዝነው ምን ?ለማለት ሲሆን ፤ አትወገር ቢልም ደግሞ የሙሴን ሥርዓት አፈረሰ ብለን እንጣላዋለን ለማለት ነው ።

መሏልስውም በጠየቁት ጊዜ ፤ ቀና ብሎ ከናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በደንጊያ ይውገራት ብሎ የየራሳቸው ኃጢአት በየግንባራቸው ላይ እንዲነ

www.ethiopianortodox.org

በብ ማድረጉም አንዱ በሌላው ላይ በቅናት ወይም በምቀኝነት መነሣት የማይገባው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው ።

## ነሐሴ ፱ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ ም እሑድ ።

ምስባክ ፤ ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ። በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወሁብርት ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ ዕዝነኪ ።

ወንጌል ዮሐንስ ። ምዕ፤ ፲ ። ቍጥር ፩ - ፳፱ ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ ወደበጐች ሥፍራ በበር የማይገባ በሌላም መን ገድ ዘሎ የሚገባ እርሱ ሌባ ወምበዴም ነው ።

በበር የሚገባ ግን እርሱ የበጐች ጠባቂ ነው ።

ለርሱም በረኛው ይከፍትለታል ፤ በጐቹም ድምፁን ይሰሙታል ፤ በጐቹንም በየስማቸው እየጠራ ያሰማራቸዋል ።

በጐቹንም ባሰማራቸው ጊዜ በፊታቸው ይሔዳል ፤ በጐቹም ይከተሉታል ፤ ድምፁን ያውቃሉና ።

ሌላውን ግን ይሸሹታል እንጂ አይከተሉትም ፤ የሌላውን ድምፅ አያውቁምና ።

ጌታ ኢየሱስም ይህን ምሳሌ ነገራቸው ፤ እርሳቸው ግን ይነግራቸው የነበረ ውን አላስተዋሉም ።

ጌታ ኢየሱስም ደግሞ አላቸው ፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ የበጐች በር እኔ ነኝ ።

ከእኔም በፊት የመጡ ሁሉ እነርሳቸው ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው ፤ ነገር ግን በጐቹ አልሰሙዋቸውም ።

እውነተኛውም በር እኔ ነኝ ፤ በእኔም የሚገባ ይድናል ፤ ይገባልም፤ ይወጣልም ፤ መሰማርያም ያገኛል ።

ሌባ ሊሠርቅና ሊያርድም ሊያጠፋም ነው እንጂ አይመጣም ፤ እኔ ግን ሕይ ወት እንዲያገኙና እጅግም ይበዛላቸው ዘንድ መጣሁ ።

እረኛ እኔ ነኝ ፤ ቸር እረኛም ፤ ስለበጐቹ ቤዛ ሕይወቱን ይለውጣል ።

እረኛ ያልሆነ በጐቹም የርሱ ያልሆኑ ምንደኛ ግን ፤ ተኵላ ሲመጣ ባየጊዜ በጐ ቹን ትቶ ይሸሻል ፤ በጐቹንም ተኵላ ይነጥቃቸዋል ፤ ይበትናቸዋልም ።

ምንደኛውስ ይሸሻል ፤ ስለበጐቹም አያዝንም ምንደኛ ነውና ፤ ቸርእረኛም እኔነኝ ፤ በጐቹንም አውቃለሁ ፤ እነሱም ያውቁኛል ።

አብም እኔን እንዲያውቀኝ እኔም አብን አውቀዋለሁ ፤ ሕይወቴንም ስለበጐቹ ቤዛ እለውጣለሁ ።

ደግሞም ከዚህ መንጋ ያይደሉ ሌሎች በጐች አሉኝ ፤ እነዚያንም አመጣቸው ዘንድ ይገባኛል ፤ ድምፄንም ይሰሙኛል ፤ ለአንድ እረኛም መንጋ ይሆናሉ ።

ስለዚህም አብ ይወደኛል ፤ እኔ መልሼ እወስዳት ዘንድ ሕይወቴን እሰጣለሁና ።



ከእኔ ማንም አይወስዳትም ፤ ነገርግን እኔ በፈቃዴ እሰጣታለሁ ፤ እኔ እሰጣትና መልሼም እወስዳት ዘንድ ችሎታ አለኝና ፤ ይኸንንም ትእዛዝ ከአባቴ ዘንድ ተቀበልሁ ።

ስለዚህም ነገር ደግሞ በአይሁድ መካከል መለያየት ሆነ ።
ከነርሳቸውም ብዙዎቹ ጋኔን አድሮበታል ፤ ፈጽሞም አብዷልና ለምን ታደምጡታ ላችሁ አሉ ? ።

ሌሎችም ይህ ነገር የጋኔን አይደለም ፤ ጋኔን የዕውሮችን ዓይን ያበራ ዘንድ ይችላልን ? አሉ ።

በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው ።

### የቃለ ወንጌሉ ምሥጢራዊ ስልት ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ ወደበጐች ሥፍራ በበር የማይገባ በሌላም መን ገድ ዘሎ የሚገባ እርሱ ሌባ ወምበዴም ነው ፤ በበር የሚገባ ግን እርሱ የበጐች ጠባቂ ነው ማለቱ እግዚአብሔር ወልድ ትንቢት ተነግሮለት እግዚአብሔር መስክሮለት ፤ ወደዚህ ዓለም በመምህርነት መምጣቱ የሚገባ ሲሆን ፤ ያለፈቃደ እግዚአብሔር እስ ተምራለሁ ብለው የመጡት ፤ ወይም የተነሡት ግን ሌቦች መሆናቸውን ሲያስረዳ ነው ።

እነዚህም እንደ ይሁዳ ዘገሊላና እንደቴዎዳስ ዘግብጽ ያሉት ናቸው ።

---

## ነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ ም እሑድ ።

ምስባክ ፤ ወተዘያነው ዳኅናሃ ለኢየሩሳሌም ።
ወፍሥሓሆሙ ለእለ ያፈቅሩ ሰመከ ።
ይኩን ሰላም በኃይልከ ።

ወንጌል ማቴዎስ፤ ምዕ ፳፮ ፤ ቍጥር ፳፮-፴፩ ።

እርሳቸው ሲበሉ ጌታ ኢየሱስም ኅብስቱን አንሥቶ ያዘ ፤ ባረከውም ፤ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ እንኩ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ ሰጠ ።

ጽዋንም ተቀብሎ አመሰገነ ፤ ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ብሎም ሰጣቸው ።

ይህ የሐዲስ ሥርዓት ኃጢአትን ለማስተሥረይ ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ ደሜነውና ።

በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋራ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ ከዚህ ከወይን ፍሬ አልጠጣም እላችኋለሁ ።

የምስጋናም መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ፤ ወደደብረ ዘይት ወጡ ።

ሰማይና ምድር ያልፋል ፤ ቃሌ ግን አያልፍም ።

### የቃለ ወንጌሉ ምሥጢራዊ ትርጉም ።

ከዚህ በላይ የተነገረው ቃለ ወንጌል እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከጠለቀ ዘለዓለማዊ ጉድጓድ ለማውጣት በቸርነቱ ብዛት ራሱ በእጁ የፈጠረውን ፈራሽ በስባሽ ሥጋ ከለበሰና በለበሰው ሥጋ ልዩ ልዩ የሆነውን መከራ ከተቀበለ በኋላ ፤ በመልዕልተ መስቀል ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ለዘለዓለም ሕይወት ይሆን ዘንድ መስጠቱ ንና በሞቱም ሞትን (ዲያብሎስን) እንዳይሽረው የሚያስረዳ ነው ።

www.ethiopianortodox.org

## ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ ም እሑድ ።

ምስባክ ፤ ወለእመኒ ፈለሱ አድባር ውስተ ልበ ባሕር ።
ደምፁ ወተሐምጉ ማያቲሆሙ ።
ወአድለቅለቁ አድባር እምኃይሉ ።

ወንጌል ማቴዎስ ምዕ ፳፩ ቁጥር ፲፰ - ፳፫ ።

በነጋውም ወደከተማ ሲመለስ ተራበ ።

በመንገድም አጠገብ በለስ አየ ፤ ወደርሷም ሔደ ፤ ከቅጠል በቀር አንዳች አላ ገኘባትም ፤ ለዘለዓለም ፍሬ አይሁንብሽ አላት ፤ በዚያም ጊዜ በለሲቱ ደረቀች ።

ደቀ መዛሙርቱም አይተው ተደነቁ ፤ እንዲህ ሲሉ ፤ በለሲቱ አሁን በአሁን እን ዴት ደረቀች ?

ጌታ ኢየሱስም መለሰ አላቸውም ፤ እውነት እላችኋለሁ ፤ እምነትስ ቢኖራችሁ ባቺጠራጠሩም በበለሲቱ እንደተደረገው ብቻ አታደርጉም ፤ ነገር ግን ይህን ተራራ ፍለስና ወደባሕር ተወርወር ብትሉት ይደረጋል ፤ በእምነትም የምትለምኑትን ሁሉ ትወስዳላችሁ ።

### ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ።

### ከወንጌሉ ምሥጢር ።

በነጋውም ወደከተማ ሲመለስ ተራበ ፤ በመንገድም አጠገብ በለስ አየ ፤ ወደእ ርሷም ሔደ ፤ ከቅጠል በቀር አንዳች አላገኘባትም ፤ ለዘለዓለም ፍሬ አይሁንብሽ አላት በዚያም ጊዜ በለሲቱ ደረቀች ያለው ቃሉ አማናዊ ነው ። ውስጠ ምሥጢሩ ግን ጌታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሲያስተምር ከሰው ፍቅር ተርቦ እሥራኤልን ማግኘ ቱን ፤ ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብሎ ቢሔድም ፤ እሥራኤል ከመሸሏ በቀር ሌላ አለማግኘቱን የሚያረጋግጥ ነው ።

በለስ ያለውም እሥራኤል መሆናቸውን ለመረዳት ፤ በለስ ዘያብቈ ቤተ እሥራኤል እሙንቱ ሲል ይገኛል ።

---

## ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ ም እሑድ ።

ምስባክ ፤ መንክር ተላህያ ለባሕር ።
መንክርሰ እግዚአብሔር በአርያሙ ።
ስምዓ ዚአከ እሙን ፈድፋደ ።

ወንጌል ሉቃስ ምዕ ፳፬ ቁጥር ፲፫ -፴፫ ተመልከት ።

### የወንጌሉ ሐተታ ።

ጌታችን ኢየሱስ ከሃርሳቸው ሁለቱን ሰዎች ባገኘ ጊዜ ፤ ንግግራቸውን ሰምቶ እናንተ አላስተዋዮች ፤ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ለማመን ልባችሁ የደነደነ ማለቱ ፤ በመጻሕፍተ ኦሪትና በመጻሕፍተ ነቢያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ሥጋን ከተቀበለ በኋላ ወደ ባሕርይ አባቱና ወደ ባሕርይ ጌትነቱ የሚመለስ ስለመሆኑ የተጻፈውንና የተነገረውን ባለማስተዋላቸው እንደሆነ ቃለ ወንጌሉ አመልክቷል ።

www.ethiopianortodox.org

የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 5.00
• ያንዱ . 0.50
ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ።